በሰሜን አሜሪካ የኢትዮጵያ ሙዚቃ ሙያተኞች ማህበር
ASSOCIATION OF ETHIOPIAN MUSICIANS IN NORTH AMERICA
1914 9th Street N.W. Suite 3 Washington, DC. 20001
Tel (202) 483 0376 Fax
www.ethiomusicians.com ethiomusicians@yahoo.com

# የኢትዮጵያ የሙዚቃ ንጉሥ ተለየን

ከያኒ ዶክተር ጥለሁን ገሠሠ በድንገት ከዚህ ዓለም በሞት የመለየቱ ዜና በሰሜን አሜሪካ የኢትዮጵያ ሙዚቃ ሙያተኞች ማህበር ጠቅላላ አባላት፤ የሥራ አመራር ክፍል እና የበላይ ጠባቂዎችን በሙሉ ያስደነገጠ መሪር ዜና ነው።

ከያኒ ጥላሁን ገሠሠ በተለያዩ ጊዜያት በህመምም ሆነ እስከ ጦር ሜዳ ድረስ ያጋጠሙትን የተለያዩ አደጋዎች በመንፈሰ ጠንካራነትና በእግዜር ድጋፍ ተቋቁሞ ለሚወደው ሕዝብ መቆየቱ ትልቅ ተስፋና አለኝታ ነበር።ዛሬ በድንገት ከመሀላችን
መለየቱ አጅግ በጣም መሪር ሀዘን የሰረጸብን መሆኑን እና ልባችን በጣም የተሰበረ መሆኑን መግለጽ ግድ ይለናል።

የኪነጥበብ አባታችን ጥላሁን ገሠሠን በሙያው የማያደንቀው ፤ በታላቅነቱ የማያከብረው ከልሂቅ እስከ ደቂቅ ከልጅ እስከ አዋቂ ድረስ በምሳሌነቱ ያልኮራበት የለም ። የጥላሁንን የህይወት ታሪክና ምግባር ዝርዝር ለታሪክ መዝጋቢዎች ትተን ለሙያው ዕድገት የከፈለውን መስዋዕትነት በተግባር የገለጸውን አርአያነት፤ ለሙያ አጋሮቹ የነበረውን ፍቅርና መመኪያነት ማሰቡ ሀዘናችንን የበለጠ መሪር አርጎታል።

ከያኒ ጥላሁን የኢትዮጵያ ሙዚቃ ሙያተኞች ንጉሥ እንደሆነ ለዘለዓለም ይኖራል። ጥላህን ዛሬ ተለየን እንጂ አልሞተም ።ስሙ ከመቃብር በላይ ፤ሥራውና ምግባሩ ህያው ነው። ለአንጋፎች መጽናኛ ለታዳጊዎች ምሳሌ እንደሆነ ይኖራል።

ለከያኒ ጥላሁን ሚመጥን ሀዘን መግለጫ እንባ፤አድናቆት መግለጫ ጭብጨባ፤ ስሜት መግለጫ ቃላት አይገኝለትም። እኛ የሙያአጋሮቹ በዚህ ሳንገታ የቆመለትን ሙያና የወደቀለትን ባንዲራ አንግበን እንደምንዘልቅ ቃል ልንገባለት እንወዳለን ።

ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ፤ ለመላ ቤተሰቦቹ ፤ ለቅርብ ዘመዶቹና ጓደኞቹ መጽናናትን ይሰጥ ዘንድ ጸሎታችን ነው።

በሰሜን አሜሪካ የኢትዮጵያ ሙዚቃ ሙያተኞች ማህበር

ጠቅላላ አባላት
የሥራ አመራር ክፍል
የበላይ ጠባቂ ኮሚቴ

http://www.tilahungesesse.org